ሴፕቴምበር 2023

ውድ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና የሥራ ባልደረቦች

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ ለተማሪዎች ያለን ቁርጠኝነት በመከባበር እና በእኩልነት ባህል ላይ የተመሰረተ ነው። የማህበረሰባችንን ብዝሃነትና ልዩነት የምናከብር ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ እና ስኬታማ የመሆን እድል እንዳለው/እንዳላት ማረጋገጥ አለብን። ይህ ቁርጠኝነት በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ውስጥ በግልጽ የተካተተ ነው፣ይሄውም ሁሉንም አካታች፣ ተቀባይነት ያለው እና ፍትሃዊ የትምህርት አካባቢን ለማበልፀግ የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነቱን ያጠነክራል። ከአድልዎ፣ከ ጉልበተኝነት እና ከትንኮሳ የጸዳ LGBTQ+ ተማሪዎቻችን ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ ቦታ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን እንገነዘባለን። ተማሪዎች የፆታ ማንነታቸውን በትክክል እና ያለ ፍርሃት መግለጽ መቻል አለባቸው፥ እናም የተለየ ማንነታቸውን እና የህይወት ተሞክሮቻቸውን ማንፀባረቅ እና ማክበር በሚቻልበት አካባቢ ለመማር እንደሚጠብቁ እናምናለን። እንደ ት/ቤቶች ዲስትሪክት፣ የፆታ ማንነት ጉዳዮችን እውቅና ለመስጠት እና ለማክበር፣ የተማሪዎችን ጥያቄዎች በምክንያታዊነት ለመመለስ እና የእያንዳንዱን ተማሪ ግላዊነት እና ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ቁርጠኞች ነን።

ይህን ወሳኝ ርዕስ የሚመለከቱ የተለያዩ የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ MCPS ደንቦችን እና አፈጻፀሞችን ለማጠናከር እና ለማብራራት፣ ይህንን አጠቃላይ መመሪያ አዘጋጅተናል። ለሰራተኞቻችን፣ ለተማሪዎቻችን፣ ለቤተሰቦቻችን እና ለማህበረሰቡ ግልጽ የሆነ መግለጫ በመስጠት እና እነዚህ መረጃዎች ሁሉ በአንድ ላይ መገኘት አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን። ይህ መመሪያ በተዘጋጀበት ጊዜ ሁሉ፣ MCCPTA-LGBTQ+ ንዑስ ኮሚቴ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በንቃት ተባብረናል፣ ለትምህርት፣ ለመልካም ግንኙነት፣ ለመከባበር፣ እና ስለ ፍትሃዊነት የላቀ እሴቶቻችን በዋጋ ሊተመን የማይቻል አስተዋጾ ያለንን ቁርጠኝነት ጥልቀት ሰጥቷል። ለእነርሱ አጋርነት እና ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ለሁሉም ተማሪዎቻችን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አወንታዊ እና መከባበር የሰፈነበት የመማሪያ አካባቢዎችን ለመፍጠር ያለንን ቁርጠኝነት ማሳደግ የምንቀጥለው በዚህ ትርጉም ባለው አጋርነት ነው።

ከአክብሮት ጋር

Monifa B. McKnight, Ed.D.
Superintendent of Schools
ሞኒፋ ቢ. ማክኒት ዶ/ር
የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

